# የ 5 ዓመቱ የዕድገትና የለውጥ ዕቅድ ይሳካ ይሆን?

*ከዮሐንስ*

ሰሞኑን በገዢው ፓርቲ ተዘጋጅቶ ለውይይት በቀረበው የ5 ዓመት የዕድገትና የለውጥ ዕቅድ ዙርያ በመሪዎቻችን እና በተለያዩ ሚድያዎች ብዙ ሲባል ሰምተናል፡፡ እንደ ሁሉ ጊዜ በዚህ ዕቅድ ላይም ጎራ የለዩ አስተያየቶች ሲሰነዘሩ አስተውያለሁ፡፡

ገዢው ፓርቲ ዕቅዱን ላሳካ እችላለሁ ሲል ተቃዋሚዎች ደግሞ እንዴት ተደርጎ፤ በየት ታልፎ ወዘተ የሚል መልእክት ያለው ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፤ የአገራችን ኢኮኖሚ በኢንዱስትሪ መመራት ማስጀመር፤ ከ ሁለት ሺህ ኪ.ሜ. በላይ የባቡር መስመር መዘርጋት፤ ተጨማሪ ስምንት ሺህ (8000) ሜጋ ዋት ኢነርጂ ማመንጨት፤ ትላልቅ የግንባታ ዕቃዎች አገር ውስጥ ማምረት፤ ከጨርቃ ጨርቅ ኤክስፖርት ከ አንድ ቢልዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘ ት.......፡፡

ገዢው ፓርቲ እነዚህ ለሰውና ለምድር የከበዱ ዕቅዶች በመጪዎቹ አምስት ዓመታት አሳካለሁ ሲል ሁሉም እንደየአቅሙ የታየውን አስተያየት መስጠቱ አይቀርም፡፡

ለገዢው ፓርቲ በማሰብ « ለምን ቀለል ያለ፤ የሚችለውንና ከሕዝቡ ጋር የማያጋጨውን ዕቅድ አይዝም» የሚሉ ቀና አሳቢዎች በአንድ በኩል፤ «ሳይደፈርስ አይጠራምና» ይሞከር የሚሉ በሌላው ገጽ፤እናውቃለን፤ ልምድ አለን ባዮች ደግሞ «የብዙ አገሮች ልምድና ተመክሮ አለን ገዢው ፓርቲ የያዘውን ዕቅድ በማንኛውም መስፈርት ዕውን ሊሆን አይችልም የሚሉ በሌላ ጎራ፤ « ይህ የመለስ ዜናዊ ህዝቡን የማደናበርያ ተንኮል» ከወዲያ ማዶ፤ ከተተገበረ ጥሩ ነው ነገር ግን አገር ውስጥ ዴሞክራሲ ሳይኖር፤ ተቃዋሚዎች በቂ ወንበር ካላገኙ አይተገበርም- የተቃዋሚ ጎራ፡፡ ብቻ ሁሉም የመሰለውን ከማቅረብ አልተቆጠበም፡፡

ከዚህም ከዚያም አስተያየት መቅረቡ ክፋት የለውም ምክንያቱም አስተያየት የሚሰጥበት ስራ ስለተሰራ ነው አስተያየት እየተሰጠ ያለውና፡፡ እኔ በተፈጥሮየ አይሆንም፤ አይቻልም ወዘተ የሚሉ አስተሳሰቦች አይመቹኝም፡፡ በአንጻሩ ለምን አይሆንም፤ ለምን አይሳካም፤ ለምን አይሞከርም፤ ማለትን እመርጣለሁ፡፡ በርግጥ አግባብነት ባለው አኳኃን የማይሆነውን አይሆንም መባል እንዳለበት አምናለሁ፡፡ ለምሳሌ አንዱ ተነስቶ « አሁን ባስመዘገብነው እድገት የተነሳ ኢትዮጵያ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ኒኩልየር ሰርታ ማስወንጨፍ ትችላለች» ቢል ምናልባት ኒኩልየር ለማስወንጨፍ ምን ምን ሂደቶች መታለፍ እንዳለባቸው ካለማወቅ የተነሳ ሊሆን ስለሚችል አይሆንም፤ አይደረግም ቢባል አግባብነት አለው፡፡ ለወደፊቱስ? ለወደፊቱማ ለምን አይቻልም በደንብ ነውእንጂ፡፡

በመሆኑም ይህ ዕቅድ ይሳካ ይሆን ወይ የሚል ጥያቄ ሲነሳ በጉዳዩ ላይ አንዳንድ ሃሳቦች ማመላለስ ጀመርኩ፡፡

እነሆ በ1969 ዓ.ም በጣት የሚቆጠሩ ባለራዕይ ወጣቶች የዛጉ ብረቶች ይዘው የአገራቸውን ሕዝብ ቀስፎ የያዘን ስርዓት አልባ አገዛዝ ለማስወገድ ተነሱ፡፡ በወቅቱ እነዚህ ልጆች በአበው ብሒል «ሰው ሆነው» አገር ያቀናሉ ብሎ ያሰበ ማንም አልነበረም፡፡ ከነሱ ውጪ፡፡

እስቲ ማን ይሙት ለግማሽ ምዕተ ዓመታት በፍጹም ሰላም አገር ለገዛ አገዛዝ እነዚህ ልጆች ገፍተው ይገረስሱታል ብሎ የትኛው ባለአእምሮ ነበር ያሰበው?

እስቲ ማን ይሙት በአፍሪካ ተወዳዳሪ ላልነበረው ሰራዊት ባለቤት አሸንፈው ይጥላሉ ብሎ የተነበየ ባለራዕይ ማን ነበር?

ወንበዴና ሽፍታ ከመባል አልፈው የሕዝቡን ልብና ቀልብ ገዝተው ህዝቡ የሚሸሽጋቸው፣ የሚንከባከባቸው፣ የሚያስብላቸው ብሎም ደግፎ ለድል የሚያበቃቸው የሕዝብ ልጆች ይሆናሉ ብሎ ያረጋገጠ ተስፈኛ ማን ነበር?

ከሰሜን አልፈው መሐል፣ ምስራቁን፣ ምዕራቡንና ደቡቡን ለትግል ያነቃንቃሉ ብሎ የሞገተ ተሟጋች ማን ነበር?

እውነት የኢትዮጵያ በብሔር መደራጀት እንደ ዩጎዝላቪያ ከመበጣጠስና እርስ በርስ ከመበላላት አልፋ የተረጋጋችና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት የምታስመዘግብ አገር ይፈጥራሉ ብሎ ያመነ ኃይል ማን ነበር? ማንም፡፡

በአንጻሩ ከውስጥም ከውጭም እረፍት የማይሰጥ የማጥፋት ዘመቻ እየወረደባቸው አንዳንዴም ከሸሪኮቻቸው ጭምር ለማመን የሚያዳግት ክህደት እየተፈጸመባቸው ሁሉንም በድል ተወጡት፡፡

እንዴት ቻሉት ቢባል መልሱ ቀላል ነው፡፡ እናሳካዋለን ብለው ተነሱ ፣በቃላቸው መሰረትም ያጋጠማቸውን ውጣ ውረድ ሁሉ ተቋቋሙ፣መሰራት የሚገባቸውን ስራዎች ሰሩ በቃ ተሳካ፡፡

በድርቅና ረሃብ ብቻ ስምዋ ይጠራ የነበረችው አገራችን ኢትዮጵያ አሁን በባለ ሁለት አሃዝ የምታድግ አገር ፣ ፈጣን እድገት ካስመዘገቡ የአፍሪካ አገሮች መካከል በሶስተኛነት የተሰለፈች አገር፣ በአለም ዙርያ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ከሚገኙ ሃያ አገሮች መካከል የተሰለፈች አገር፣ በተባበሩት መንግስታት የተቀረጸው የሚሌንየም የእድገት ግብ ሊያሳኩ ከሚችሉ ጥቂት አገሮች አንዷ ለመሆን በቃች፡፡

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኃላ የአሜሪካ መሪዎች «MAN ON THE MOON» ብለው ዕቅድ ሲያወጡ ለየላቸው አበዱ ተብለው ነበር፡፡ በርግጥ ከአፍንጫው አርቆ ለማያስብ ጨረቃ ላይ ሰው ማድረስ ቅዠት ነው፡፡ በአንጻሩ በተግባር ለሚያምኑ ደግሞ ሊሆን የሚችል ግን ብዙ ስራ የሚጠይቅ ዕቅድ ነው፡፡

እርግጥ መሪዎቹ ሰውን በጨረቃ ላይ የማድረሱ ዕቅድ ተናግረው እና በዕቅድ ብቻ ይዘው ዝም አላሉም፡፡ አበይት ሊባሉ የሚችሉ የፖለቲካ ውሳኔዎች ወስነው ነበር፡፡ ከነዚህ ውሳኔዎች አንዱ የስርአተ ትምህርት ትኩረት ከማህበራዊ ሳይንስ ወደ ምህንድስናና ተፈጥሮአዊ ሳይንስ እንዲዞር ማድረግን ነበር፡፡ እናም በመጨረሻ ዕቅዳቸው አሳኩ፡፡

ታድያ አሁን በኢህአዴግ የቀረበው ዕቅድ ለምን አይሳካም? ከዕቅዱ ጋር የተመጣጠነ ትግበራ ካለ ግጥም አድርጎ ይሳካል እንጂ፡፡

የፎርድ መኪና ባለቤት ሄነሪ ፎርድ እንዲሁ በዘመኑ «A CAR IN EVERY GARAGE» የሚል መፈክር ይዞ ተነስቶ ነበር፡፡ ባለሁለት ጎማ ተሽከርካሪ ብርቅ በሆነበት ዘመን በእያንዳንዱ ጋራዥ መኪና ማስገባት ከብዙ መስፈርቶች አኳያ ራዕይ ለሌለው ሰው የማይታሰብ ነው፡፡ ሃያ እና ሰላሳ ዓመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ግን አንድ መኪና ብቻ ሳይሆን ለመቁጠር እስከሚያስቸግር ብዛት ያላቸው መኪናዎች በየአገሩ ይርመሰመሱ ጀመር፡፡

ታድያ በልማት መስመር ላይ ላለ አገር፣ እንዴት ልማት ማምጣት እንደሚቻል ከራሱ ልምድ ያረጋገጠ አገርና አመራር ያወጣው ዕቅድ ለምን አይሳካም? ይሳካል እንጂ!

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ይህን የመሰለ አንጆት አርስ ዕቅድ ለምን ተቃውሞ አጋጠመው የሚል::

በእኔ እምነት ተቃዋሚዎቹን በሁለት ወገን መመደብ ያለባቸው ይመስለኛል:: አንደኛው ምድብ ቢያንስ በስም ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ ሆነው በተቃውሞ ጎራ የተሰለፉ ሲሆኑ ሁለተኛው ምድብ ደግሞ የውጭ ኃይሎች የያዘ ምድብ::

የመጀመርያው ቡድን የኃላ ታሪክ ሲታይ አብዛኛዎቹ ከንጉሱ ጊዜ ጀምረው ስልጣን ላይ ያለውን ገዢ መቃወምን እንደ ዋና ተግባር የያዙ ሰዎች ናቸው:: እነዚህ አካላት መቃወም የሚያቆሙት ስልጣን ላይ ሲወጡ ብቻ ነው:: ስልጣን ላይ ለመውጣት ደግሞ ምኞት ብቻ በቂ አይደለም:: መነሻና መድረሻ ያለው ቁልጭ ያለ ዕቅድ ያስፈልጋል:: በዕቅዱ መሰረት ደግሞ ሳይታክቱ መስራት የግድ ይላል::

በዚህ ቡድን የታቀፉት አካላት ከዚህ አንጻር ሲመዘኑ ዕድሜ ልካቸው ፓርቲ ሲያቋቁሙ፤ ሲያፈርሱ፤ ስም ሲለውጡ፤ሲሰነጠቁ፤ ህብረት ፈጠርን ብለው እንደገና ሲበተኑ አልፎ አልፎም የሽምቅ ውጊያና የሽብር ተግባር ቢያከናውኑም አንድም ጊዜ የሚፈልጉትን አሳክተው የማያውቁ ናቸው:: የሚያስቡትና የሚያቅዱት ሁሌም ፋርሽ ስለሚሆንባቸው ሌላ ፓርቲ የሚያቀርበውን ዕቅድ አይሳካም፤ አይሆንም ማለትን ያስቀድማሉ:: ሰው የሚያስበው ከልምዱና ከአስተዳደጉ ወዘተ አንጻር ስለሆነ አንድም ጊዜ ዕቅድ አሳክቶ የማያውቅ ቡድን የሌላውን ዕቅድ አይሳካም ቢል ተአምር አይሆንም:: ከልምዳቸው አንጻር ጭንቅላታቸው የሚያውቀው የማይሆነውን ፤ የማይሳካውን፤ ፋርሽ ዕቅድ፤ ፋርህ ፖለቲካ፤ ፋርሽ ተቃውሞ፤ ፋርሽ ኑሮ፤ ወዘተ ነው ::

ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ድጋፍ አይደረግ፤ እርዳታ አይሰጥ፤ ግድብ አይሰራ ወዘተ የሚል ኢትዮጵያዊ በመጀመርያ ስለ ኢትዮጵያዊነቱ እርግጠኛ መሆን ይገባል:: ኢትዮጵያዊ መሆኑን እርግጠኛ ከሆንን በኃላ ግን የጎደለበት ብሎን መኖሩን መተማመን አለብን:: ምክንያቱም ኢትዮጵያን የሚቃወም ኢትዮጵያዊ ለኔ አይገባኝም:: የተለየ የፖለቲካ አቋም መያዝ፤ ስልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ አካሄድ አለመደገፍና አማራጭ ይዞ መቅረብ የነበረና የአባት ስራ ነው:: የራስን አገር ልማት መቃወም ግን ትርጉሙን ፈልጌ ላገኘው አልቻልኩም::

ሁለተኛው ቡድን የኢትዮጵያን ዕድገትና ስልጣኔ የማይፈልጉ፤ በጥርጣሬ አይን የሚያዩ ወይም ሲፈቅዱልን ብቻ የምናድግ እስከዚያው ድረስ ግን ባለህበት ሂድ እየተባልን እንድንቆይ የሚፈልጉ አካላት የተሰበሰቡበት ቡድን ነው::

እነዚህ አካላት አነሰም በዛም የሚቃወሙት ጥቅማቸው ስለተነካ ወይም ጥቅማችን ይነካብናል ብለው ስለሚያስቡ ነው:: ኢትዮጵያ ካደገች እንደ ድሮ አትታዘዘንም፤ እናም ጥቅማችንን ለማስጠበቅ ፍላጎታችንን መጫን አንችልም ከሚል ጽንፍ ከያዘ ምክንያት የተነሳ ሊቃወሙ ይችላሉ::

በኔ እምነት የተዋጣለት እና ቀጣይነት ያለው የአገሮች ጤነኛ ግንኙነት የሚኖረው አንዱ በማስፈራራት ሌላኛው በመፍራት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሲኖር ብቻ ነው ::

ፍላጎትን በሃይል የመጫን ፍልስፍና ጊዜ ያለፈበትና ዘለቄታ የሌለው አማራጭ ነው:: በያዝነው ክፍለ ዘመን አማራጭ በማሳጣት፤ በመከልከል፤ በመቃወምና በማተራመስ ዘዴ ሌላውን መቆጣጠር አዳጋች እየሆነ እንደመጣ በአለማችን ዙርያ ከምናያቸውና ከምንሰማቸው እውነታዎች መገንዘብ የሚቻል ይመስለኛል::

ያም ሆኖ የአገራችንን ልማት የሚቃወሙ የውጭ ኃይሎች ይህንን ተገንዝበው ባይተገብሩትም እነሱን እየታገልንም ሆነ ጆሮ ዳባ ልበስ እያልንም መቀጠል አለብን ባይ ነኝ:: «ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሉ ግን መንገዱን አያቆምም» እንዲሉ::

የውጪ ኃይሎች የራሳቸውን አጀንዳ ይዘው ሲንቀሳቀሱ እኛ ኢትዮጵያንም የአገራችንን የልማት አጀንዳ አንግበን መነሳት አለብን የሚል እምነት አለኝ:: ይህ ወቅት ኢትዮጵያችን የምትለወጥበት ወቅት ነው:: ስማችንን የምናድስበት፤ በአፍሪካ እና በዓለም መድረክ የነበረንን የመሪነት ሚና መልሰን የምንይዝበት ወቅት ነው:: በዚህ ታሪካዊ ወቅት ባለድርሻ አለመሆን ጸጸቱ ከባድ የሚሆን ይመስለኛል::

በኔ በኩል ቢያንስ አንድ ነገር አድርጌያለሁ:: በአገራችን ግድቦች ለመስራትና ተያያዥ ወጪዎች ለመሸፈን  ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ መብራትና ኃይል ኮርፖሬሽን ያወጣው የሚለንየም ቦንድ ትንሽም ብትሆን ገዝቼ ባለሼር ሆኛለው:: ለወደፊቱም አቅሜ በፈቀደ እቀጥልበታለሁ:: ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም ነውና ነገሩ::

መጽሐፍ ቅዱስ ሳነብ ያገኘሁት አንድ ታሪክ ላውጋችሁ አስቴር የተባለች ባለታሪክ የንጉስ ሚስት ትሆን ዘንድ ተመርጣ ቤተመንግስት ትገባለች:: በዚያን ወቅት ታድያ ንጉሱ በክፉ መካሪዎች ተገፋፍቶ የአስቴርን ወገኖች ለማጥፋት ይነሳሳል:: በዚህ ጊዜ ለመጥፋት ከተፈረደባቸው ወገኖች አንዱ አስቴርን እንዲህ አላት:: «በታሪክ አጋጣሚ ወገኖችሽን ከምታድኚበት ቦታ ላይ ተቀምጠሻል:: ንጉሱ ዘንድ ግቢና ስለወገኖችሽ ምልጃ አቅርቢ:: ይህን ባታደርጊ ፈጣሪ ሕዝቡን ያድናል» አላት:: አስቴርም በዚህ ማሳሰቢያ ተነሳስታ ስለወገኖችዋ ምልጃ አቅርባ ወገኖችዋን ከጥፋት አዳነቻቸው::

እንግዲህ መንግስት የቤት ስራውን ሰርቶ አቅርቦልናል:: ለዕቅዱ ስኬታማነትም አብረን እንስራ የሚል ጥሪ አቅርቧል:: በ19 ዓመታት ቆይታው እንዳየነው አልፎ አልፎ ወደ ኃላ የመመለስ አዝማምያዎች ቢስተዋሉም ኢህአዴግ አንድን ጉዳይ እተገብራለሁ ብሎ ቆርጦ ከተነሳ ማሳካት እንደሚችል በተግባር አሳይቷል:: አሁን የተያዘውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ ሁሉም የበኩሉን መወጣት እንዳለበት ጥርጥር የለውም:: የአገራችንን ገጽታ በእጅጉ ሊለውጥ በሚችለው በዚህ ዕቅድ ስኬት ለመሳተፍ በታሪክ አጋጣሚ ተገኝተናል:: በመሆኑም ለዚህ ዕቅድ እውን መሆን መረባረብ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የውዴታ ግዴታ ነው ብየ አምናለሁ:: አልሳተፍም፤ እቃወማለሁ የሚል ካለ የራሱ ጉዳይ ነው:: ኢህአዴግ እንደሆነ ከማሳካት ወደኃላ አይልም::

ታድያ በዚህ አጋጣሚ ውጪ አገር የምንኖር ወገኖች ለምን አንድ ሃሳብ ይዘን መንግስታችን ዘንድ አንቀርብም? ይህንን አንጀት አርስ ዕቅድ ዕውን ለማድረግ ከኛ ምን ይጠበቃል? መንግስትን በምን መልኩ እንርዳ? የሚል ሃሳብ! ምላሻቹህን እጠብቃለሁ:: ሰላም::